# በኣካል ተገኝተው ለማይመርጡና ከቀኑ በፊት ለመምረጥ ለሚፈልጉ የሚሰጥ የ2016 የማመልከቻ ፎርም

**በኦንላይን http://www.mnvotes.org በመግባት ኣመልክቱ** *ወይም*

**ከታች ከቁጥር 1 እስከ ቁጥር 7 ያሉትን መስመሮች ያጠናቅቁ። በግልጽ እንደሚታይ ኣርገው ይጻፉ።**

ይህንን ፎርም በተቻለ መጠን በፍጥነት ሞልተው ይላኩ። የምርጫ ወረቀቶች እንዲቆጠሩ፡ በምርጫው ቀን ወይም ከዛ በፊት፡ መድረስ ኣለባቸው።

**ኣስፈላጊ፡** በኣገልግሎት ላይ ያሉ ወታደሮች ወይም ከኣገር ውጭ የሚገኙ መራጮች ይህንን ፎርም መጠቀም የለባቸውም። ለበለጠ መረጃ የዚህን ፎርም በስተጀርባ ይመልከቱ።

**1.** በኣካል መገኘት ለማይችሉና ከግዜው በፊት መምረጥ ለሚፈልጉ የተዘጋጀው ፎርም ከስር ለተጠቀሱት ምርጫዎች ሊላክ ይችላል። *(ምርጫ የማይካሄድ ከሆነ፡ ለሚቀጥለው ምርጫ ፎርሙ ሊላክ ይችላል)*

- ለመጀመርያው የማጣርያ(primary)ምርጫና ለዋናው ኣጠቃላይ ምርጫ
- ለመጀመርያው የማጣርያ(primary) ምርጫ ብቻ
- ለዋናው ኣጠቃላይ ምርጫ ብቻ
- ለልዩ የማጣርያ ምርጫ - ቀኑ ይዘርዝር
- ለልዩ ምርጫ - ቀኑ ይዘርዝር

**2.**

| የኣባት ስም | ስም | የማህል ስም | ተቀጥያ |
|---|---|---|---|
| | | | |

**3.**

| የተወለዱበት ዕለት (ወር/ቀን/ዓም) | የሚኖሩበት ኣውራጃ | የስልክ ቁጥር - - |
|---|---|---|
| | | |

| የኢሜል ኣድራሻ |
|---|
| |

**4.** በሚመለከትዎ ሳጥኖች ላይ ምልክት ያድርጉ፡

- የሚኖሶታ የመንጃ ፍቃድ ኣለኝ ወይም የሚኖሶታ የመታወቅያ ወረቀት ኣለኝ። ቁጥሩም፡
- የሶሻል ሴኩሪቲ ቁጥር ኣለኝ የዚህ ቁጥር የመጨረሻዎቹ ኣራት ቁጥሮች፡ XXX-XX-
- የሚኖሶታ የመንጃ ፍቃድም ሆነ የሚኖሶታ የመታወቅያ ወረቀት ወይም የሶሻል ሴኩሪቲ (social security) ቁጥር የለኝም።

የመታወቅያ ወረቀትዎ ቁጥር፡ በአካል ተገኝተው ለማይመርጡና ከቀኑ በፊት ለመምረጥ ለፈለጉ (absentee ballot) ሰዎች በሚላክ የምርጫ ፖስታ ላይ ካለው ቁጥር ጋር ይነጻጸራል።

**5.**

| የሚኖሩበት ቤት ኣድራሻ(የመኖርያ ቤት) | የቤት ቁጥር | ከተማ | | የከተማ ክልል ቁጥር (ዚፕ ኮድ) |
|---|---|---|---|---|
| | | | **MN** | |

**6.**

| በኣካል ተገኝተው ለማይመርጡና ከግዜው በፊት ለሚመርጡ ሰዎች የምርጫ ፎርሙ የሚላክበት ኣድራሻ | የቤት ቁጥር | ከተማ | ክፍለሃገር | የከተማ ክልል ቁጥር (ዚፕ ኮድ) |
|---|---|---|---|---|
| | | | | |

**7.** ከዚህ በታች በዝርዝር የሰፈሩት ሁሉ ትክክል መሆናቸውን ኣረጋግጣለሁ፡

- ይህንን ፎርም የምሞላው ለራሴ በራሴ መሆኑን
- ምርጫ በሚካሄድበት ቀን ቢያንስ ቢያንስ ዕድሜዬ 18 ዓመት መሆኑን
- ዜግነቴ ኣሜሪካዊ መሆኑን
- ከምርጫው ቀን በፊትና እስከ ምርጫው ቀን ድረስ በሚኖሶታ ውስጥ ለ20 ቀናት እንደተቀመጥኩ
- በዚህ ፎርም ላይ በተጻፈው ኣድራሻ እየኖርኩ መሆኔን
- በፍርድ ቤት በታዘዘ ብይን፡ ምርጫ እንዳልመርጥ እንዳልታገድኩና በፍርድቤት በተበየነ ቁጥጥር/ጥበቃ ላይ እንዳልሆንኩ
- በፍርድቤት፡ ለመምረጥ በህግ ብቁ ኣይደለም ተብሎ እንዳልተፈረደብኝ
- ለመምረጥ መብት ኣለኝ ምክንያቱም ከኣሁን ቀደም በወንጄል የተከሰስኩ ብሆንም በኣሁኑ ግዜ የተበየነብኝ የግዜ ገደብ ኣልፏል/ ተጠናቋል ወይም ከተበየነብኝ ፍርድ ነጻ እንደሆንኩ
- ይህንን የተጻፈውን ሁሉ እንዳነበኩና በደንብ እንደገባኝ፡ ከላይ የተጻፈው ሁሉ ትክክለኛ መሆኑን፡እንዲሁም ከዚህ ከተጻፈው ውስጥ ትክክል ያልሆነ የውሸት ቃል ቢገኝበት በ5 ዓመታት እስራት ወይም በ10,000ዶላር መቀጮ ወይም በሁለቱ ልቀጣ እንድምችል ተገንዝቤ ነው ይህንን ፊርማዬን የማሰፍረው።

**እዚህ ላይ ይፈርሙ፡ X**_______________________________________ **ቀን** ______/______/______

**በስተጀርባ በሚገኘው ገጽ ላይ፡ ኣካለስንኩላን መራጮች ስለሚከተሉዋቸው መመሪያዎችና ውክልና ስለመስጠት ተመልከቱ።**

official use only

| | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| Primary → ☐ reg ☐ non-reg | received date | ballot issued date | initials | type M C HCF | reason replaced ☐ rejected ☐ lost ☐ spoiled ☐ never received | repl. date: | precinct |
| General → ☐ reg ☐ non-reg | received date | ballot issued date | initials | type M C HCF | reason replaced ☐ rejected ☐ lost ☐ spoiled ☐ never received | repl. date: | school district |

**ይህንን ፎርም በተቻለ መጠን በአፋጣኝ ወደ ሚመለከተው አካል ይላኩ**

**ፎርሙን የት መላክ እንዳለቦት**

ይህንን ፎርም ከሞሉ በውሃላ ወደ ቀበሌዎ የምርጫ ጣብያ ይላኩ። ይሄው ኣድራሻ ከላይ ካልተጠቀሰ፡ የምርጫ ጣብያዎ የት መሆኑን ለማወቅ በኦን ላይን http://www.mnvotes.org በመግባት "የምርጫ ባለስልጣን የስም ማውጫ" "Election Official Directory" ስር ሊያገኙት ይችላሉ።

**በኣካል ተገኝተው ለመምረጥ ለማይችሉ ሰዎች የሚሞላውን ፎርም መልሶ ለመላክ ያሉት ሌሎች ኣማራጮች**

የመላው ኣገር ፡ የክፍለሃገር ወይም የቀበሌ ምርጫ ሲሆን፡ በኦን ላይን http://www.mnvotes.org ውስጥ በመግባት ፎርሞን ይምሉ። ወይም በወረቀት ላይ የተሞላ ማመልከቻ ፎርም በፖስታ፡ በፋክስ ወይም ከኢሜል ጋር በተያየዘ ኣባሪ ፎርም መላክ ይቻላል።

**የምርጫው ፎርም መቼ እንደሚላክሎት**

በኣካል ተገኝተው ለማይመርጡ ወይም ከቀኑ በፊት ለሚመርጡ፡ ፎርሙ የሚላክላቸው ምርጫው ከሚካሄድበት ከ45 ቀናት በፊት ነው ።(ይህ ግን በመጋቢት ወ ርየሚካሄደውን የከተሞች ምርጫ ኣይመለከትም። ለዛ ጉዳይ ፎርም የሚላከው ከምርጫው ዕለት ከ30 ቀናት በፊት ነው )። ፎርሙ እንዲላክልዎት ከዚህ ቀን በውሃላ ከሆነ የጠየቁት፡ ማመልከቻዎ በሚመለከተው የምርጫ ጣብያ እንደደረሰ ፎርሙ ይላክሎታል። ፎርሙን ካላገኙ፡ የምርጫ ቀበሌዎን እንዳልደረሶት ያመልክቱ። ጉዳዮ ምን ላይ እንደደረሰ ለማወቅ ደግሞ በኦንላይን http://www.mnvotes.org ገብተው ይጠይቁ።

**ግለኛነትን የሚመለክት ማስታወቅያ**

የተወለዱበት ዕለት፡ የኢሜል ኣድራሻዎ፡ ለሚኖሶታ የሚሰጡት የማንኛውም የመታወቅያ ወረቀት ቁጥር (የሚኖሶታ የመንጃ ፍቃድ፡ የክፍለሃገር መታወቅያ ወረቀት፡ የሶሻል ሴኩሪቲ ካርዶ የመጨረሻዎቹ ኣራት ቁጥሮች) የግሎ ናቸው። በመሆናቸውም የኣስመራጭ ኮሚቴ ባለስልጣኖች ብቻ ናቸው የሚያዩዋቸው።

የኣስመራጭ ኮሚቴ ባለስልጣኖች የተወለዱበትን ዕለት የሚጠይቁት፡ ማመልከቻዎን፡ በመራጮች መዝገብ ላይ ካለው ዕለት ጋር ለማወዳደር እንዲችሉ ነው። የተወለድኩበትን ዕለት ኣልሰጥም ካሉ ግን በኣካል ለማይመርጡና በግዜ ለመምረጥ ለሚፈልጉ ሰዎች የሚሰጠውን የምርጫ ወረቀት የማግኘት ዕድል የሎትም።

የኣስመራጭ ኮሚቴ ባለስልጣኖች ኢሜልዎን የሚጠይቁበት ምክንያት ስለዚሁ ማመልከቻዎ ለመጻጻፍ እንዲችሉ ነው። በተጨማሪም የክፍለሃገሩ የኣገር ውስጥ ኣስተዳደር ጽሕፈት ቤት ስለምርጫም ሆነ ስለድምጽ መስጠት ወይም በህዝብ በኩል ስላለው ኣመለካከት( በሌላ መንገድም ሊያገኙዎ ይችላል) ጥያቄ ሊያቀርብልዎ ሊፈልግ ይችላል። የኢሜል ኣድራሻዬን ኣልሰጥም ካሉ ግን በኣካል ቀርበው ለማይመርጡና ከግዜው በፊት ለሚመርጡ የሚሰጠውን ፎርም በኦን-ላይን ለመሙላት ኣይችሉም። ግን በወረቀት/በፖስታ ማመልከት ይችላሉ ማለት ነው።

የኣስመራጭ ኮሚቴ ባለስልጣኖች የመታወቅያ ወረቅት ቁጥሮን የሚጠይቁበት ምክንያት ድምጹን የሚሰጠው ግለሰብ፡ ማመልከቻውን ካቀረበው ሰው ጋር ኣንድ መሆኑን ለማረጋገጥ ነው።የመታወቅያ ካርድ ቁጥር እያሎት ኣልሰጥም ካሉ፡ በኣካል ተገኝቼ ለመምረጥ ኣልችልም ብለው ያቀረቡት የምርጫ ማመልከቻ ተቀባይነት ላያገኝ ይችላል። በኦንላይንም ጥያቄዎ ምን ላይ እንደደረሰ ለማወቅ ኣይችሉም።

በማምልከቻዎ ፎርም ላይ የሰፈረው ሌላው መረጃ ሁሉ ግን ምርጫን በሚመለከት እንዲሁም ለፖለቲካዊ ጉዳዮች ወይም ህግን የማስከበር ጉዳዮችን በተመለከተ ለመጠቀም ለህዝብ ክፍት ነው።የመረጃዎቹ ለህዝብ ክፍት መሆን ግን ለግል ደህንነቴ ኣስጊ ነው የሚሉ ከሆነ ግን በስልክ ቁጥር 1-877-600-8683 በመደወል ምን ማድረግ እንደምትችሉ ተረዱ።

**ማነው የምርጫ ወረቀት ለማግኘት ማመልከት የሚችለው?**

እያንዳንዱ ሰው ለራሱ ነው ማመልከት የሚችለው። በኣካል መገኘት የማይችሉና ከምርጫው ቀን በፊት ለመምረጥ የሚፈልጉና፡ የምርጫ ወረቀት እንዲላክላቸው በሚያመለክቱ ሰዎች ማመልከቻ ላይ እውነት ያልሆነ ነገር መጻፍ፡ ህጋዊ ያልሆነ የምርጫ ወረቀት ማቅረብ፡ ወይም ህጋው ያልሆነ የምርጫ ወረቀት እንዲያቀርብ ሌላ ሰውን መርዳት በህግ ያስቀጣል።

**ህጋዊ በሆነ የመኖርያ ኣድራሻዬ ካልተመዘገብኩ፡**

ለመምረጥ ኣልተመዘገብኩም ማለት ነው የሚል ኣስተሳሰብ ካሎት፡ ከምርጫ ወረቀቶችዎ ጋር የመራጭ መመዝገብያ ፎርም ኣብሮ ይላክሎታል።

**በውትድርና ዓለም ውስጥ ላሉና ከኣገር ውጭ የሚገኙ መራጮችን በተመለከተ የተሰጠ መረጃ**

እርስዎ ወይም ቤተሰብዎ በውትድርና ስራ ውስጥ ስላሉ ወይም ከኣገር ውጭ ወይም ከኣሜሪካን ኣገር ክልል ውጭ ባሉ ኣገሮች ውስጥ ስለሚገኙ፡ በኣካል ለማይገኝ ሰውና ከምርጫው ቀን በፊት መምረጥ ለሚፈልጉ ሰዎች የሚላከ የምርጫ ወረቀት እንዲላክልዎ ካመለከቱ፡ ይህንን ፎርም ኣይምሉ። የፌዴራል ፖስትካርድ ማመልከቻ (the Federal Postcard Application) በመጠቀም ካመለከቱ፡ ልዩ የሆነ ጥበቃ ለማግኘት መብት ኣሎት። ስለዚሁ ጉዳይ የበለጠ መረጃ ለማግኘት http://www.mnvotes.org ጎብኙ

**የኣካል ስንክልና ካለቦት ያሎት ምርጫዎች የሚከተሉት ናቸው፡**

- ፎርሙን ራስዎ ይፈርሙት
- በፎርሙ ላይ የራስዎን ምልክት ያድርጉ
- እርሶ ባሉበት ሌላ ሰው እንዲፈርምልዎ ይጠይቁ (የፈረመሎት ሰው የራሱን ፊርማም ኣብሮ እንዲያሰፍር ይጠይቁ)
- ፊርማዎን ባንዳች ቴምበር ዓይነት ኣስፍረው ቴምብሩን በመምታት የሚፈርሙ ከሆነ ኣሁንም እሱኑ ለመጠቀም ይችላሉ ወይም ደግሞ ሌላ ሰው እርስዎ ባሉበት ያንን የስዎን ቴምበር ሊመታሎት መጠየቅ ይችላሉ (የሚኖሶታ ህገ-መንግስትን ቁጥር 645.44 ክፍል 14 ን ይመልከቱ)

**ውክልናን በተመለከተ የተሰጠ መረጃ**

ውክልና ምርጫን ኣይመለከትም። ውክልና የሚመለከተው ንብረትንና ንብረትን የሚመለከቱ ጉዳዮችን ብቻ ነው። ውክልና የሰጡት ሰው፡ እርስዎ በኣካል በተገኙበት ቦታ ሁኖ ስለርስዎ ሊፈርም ይችላል። (የሚኖሶታ ሕገ መንግስት፡ ክፍል 523.24፡ ክፍል 14 ን ይመልከቱ)